የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ጥር ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.20
ADDIS ABABA 21st January, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፮/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የስፖርት ኮሚሽንን ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀት መወሰኛ እና የብሔራዊ ስፖርት ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ …………….ገጽ ፲ሺ፱፻፩

## Content

Proclamation No. 446/2019

Definition of Powers, Duties and Organization of the Sports Commission and the National Sports Council Establishment Council of Ministers Regulation ........................................--Page 10901

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፮/፪ሺ፲፩**

**<u>የስፖርት ኮሚሽንን ስልጣን፣ተግባርና አደረጃጀትን ለመወሰን እና የብሔራዊ ስፖርት ምክር ቤትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፴፪/፬ መሰረት የስፖርት ኮሚሽን የተቋቋመ በመሆኑ፤

የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባር የሚወስን ደንብ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአገር አቀፍ ደረጃ ስፖርትን ለማስፋፋትና ሕዝባዊ ለማድረግ ስፖርቱን በበላይነት የሚመራ ብሔራዊ የስፖርት ምክር ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፴፬ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 446/2019**

**<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE POWERS, DUTIES AND ORGANIZATION OF SPORT COMISSION AND ESTABLISHMENT OF THE NATIONAL SPORT COUNCIL.</u>**

WHEREAS, the Sport Commission has been established as per Article 32(4) of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/2018;

WHEREAS, it is necessary to issue Regulation which define powers and duties of the Commission;

WHEREAS, it is necessary to establish the National Sports Council which ensure overall organization and management of sport is community based;

NOW, THEREFORE, this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/2018.

፩. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ ደንብ «የስፖርት ኮሚሽንን ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀት መወሰኛ__ እና የብሔራዊ ስፖርት ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፮/፪ሺ፲፩» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>**ትርጓሜ**</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ ‹‹ሚኒስቴር›› ወይም ‹‹ሚኒስትር›› ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፪/ ‹‹ኮሚሽን›› ወይም ‹‹ኮሚሽነር›› ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የስፖርት ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር ነው፤

፫/ ‹‹ምክር ቤት›› ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ መሰረት ስፖርቱን ለመምራት የተቋቋመ ብሔራዊ የስፖርት ምክር ቤት ነው፤

፬/ ‹‹ክልል›› ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀፅ ፵፯ /፩/ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ነው፤

፭/ ‹‹ከተማ አስተዳደር›› ማለት የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ናቸው፤

፮/ ‹‹የስፖርት ማህበር›› ማለት የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ በወጣው መመሪያ መሰረት የተቋቋመ የስፖርት ማህበር ነው፤

፯/ በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፫. <u>**ዋና መሥሪያ ቤት**</u>

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

፬. <u>**የኮሚሽኑ ዓላማ**</u>

፩/ የኮሚሽኑ ዓላማ ከአጠቃላይ ህብረተሰቡ የስፖርት እንቅስቃሴ በመነሳት በተለይ የወጣቱን ትውልድ ግንዛቤና ተሳትፎ በማጠናከር ስፖርት ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ማድረግ እና የላቀ ችሎታ ያላቸውን ምርጥ ስፖርተኞች በማፍራት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ፤

1. <u>**Short Title**</u>

This Regulation may be cited as the "Definition of Powers, Duties and Organization of the Sports Commission and the National Sports Council Establishment Council of Ministers Regulation No. 446/2019".

2. <u>**Definition**</u>

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Ministry" Or "Minister" .means the Ministry or Minister of Culture and Tourism, respectively;

2/ "Commission" or "Commissioner" means the Commission or the Commissioner of sport, respectively;

3/ "Council" means a national Council which established to direct the sport pursuant to Article 9 of this Regulation;

4/ "Region" means any region referred to in Article 47/1/ of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution;

5/ "City Administration" means Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

6/ "Sport Association" means any National sport association certified by the Commission;

7/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>**Head Office**</u>

The Commission shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

4. <u>**Objectives**</u>

1/ The objectives of the Commission shall be to register great achievements of international standard by taping the overall sports activity within the community and in particular by creating awareness and participation of the youth and make the sport community base;

፪/ ስፖርት በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲጎለብት በማድረግ ስፖርት ለሰላም፣ ለሀገራዊ አንድነትና ወዳጅነት እና ጤናማ ትውልድ ለመፍጠር ያለውን ፋይዳ ማጉላት፤

፫/ በህብረተሰቡ መካከል ያለአድሎ እኩል የመሳተፍ መልካም መንፈስን ማዳበር ይሆናል፡፡

## ፭. <u>የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀፅ ፴፪/፬/ መሰረት ለስፖርት ኮሚሽን የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ፡-

፩/ የሀገሪቱን የስፖርት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች በስራ ላይ ያውላል፡፡

፪/ የስፖርት ማህበራት ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ የሚውል ገቢ ማመንጨት እንዲችሉ ከዓላማቸው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሥራዎች እንዲያከናውኑ ይፈቅዳል፤

፫/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቆችና መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ድጋፍ ይሰጣል፣ ከውጭ የሚገቡበትንም ሁኔታ ያመቻቻል፤

፬/ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮች ሲዘጋጁና ሲካሄዱ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፭/ ብሔራዊ የስፖርት ልማት ፈንድ በሕግ የሚቋቋምበትን ስልት ይቀይሳል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፮/ የሀገሪቱን የስፖርት መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፤ ያሰራጫል፤

፯/ የስፖርት ፋሲሊቲዎች የሚተዳደሩበትን ስልት ይቀይሳል፤

፰/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ሥም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፱/ ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## ፮. <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

ኮሚሽኑ፡-

፩/ ብሔራዊ የስፖርት ምክር ቤት፤

፪/ በመንግሥት የሚሾሙ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር፤ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

2/ by promoting sport in the community foster it role for peace, social integrity and unity and developing healthy generations;

3/ foster a spirit of goodwill and equality among all people without any discrimination.

## 5. <u>Powers and Duties of the Commission</u>

Without prejudice to Article 32/4/ of the Proclamation No, 1097/2018, the Commission shall have powers and duties to:

1/ Implement the country's sport policy and Strategy;

2/ Authorize sports associations to engage in income generating activities which are consistent with their objectives with a view to meet their financial requirements;

3/ Provide support for domestic production of sports wear and equipment and facilitate it's importation in collaboration with the concerned organs;

4/ Provide necessary support in organizing and conducting National and International sport games;

5/ Devise mechanisms for the establishment of national sports development fund by law, and implement same upon approval;

6/ Collect, compile, and disseminate the sport data of the country;

7/ Device mechanisms for administration of sport facilities;

8/ Own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

9/ Perform such other functions to achieve its objectives.

## 6. <u>Organization of the Commission</u>

The Commission shall have:

1/ National Sports Council;

2/ Commissioner and, deputy Commissioner appointed by the government; and

3/ The necessary staff.

**፯. የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት የኮሚሽኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀትና ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል፤

ረ) የኮሚሽኑን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

፫/ ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

**፰. የምክትል ኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር**

ምክትል ኮሚሽነሩ፡-

፩/ የኮሚሽኑን ተግባራት በማቀድ ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ያግዛል፤

፪/ በኮሚሽነሩ ተለይቶ የሚሰጠዉን የሥራ ዘርፍ ያከናዉናል፤

፫/ ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሰራል፡፡

**፱. መቋቋም**

ብሔራዊ የስፖርት ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ « ምክር ቤት» እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ፡፡

**7. Powers and Duties of the Commissioner**

1/ The Commissioner shall be the chief executive officer of the Commission and shall direct and administer the activities of the Commission.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the Commissioner shall:

a) Exercise the powers and duties of the Commission specified under Article 5 of this Regulation;

b) Employ and administer employees of the Commission in accordance with the federal civil service laws;

c) Prepare the annual plan and budget of the Commission and implement same upon approval;

d) Effect expenditure in accordance with the approved budget and plan of the Commission;

f) Represent the Commission in all its dealings with third parties;

g) Submit audit reports and reports on the activities of the Commission to the Ministry.

3/ The Commissioner may delegate part of his power and duties to other officials and employees of the Commission to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Commission.

**8. Power and Duties of Deputy Commissioner**

The Deputy Commissioner shall have the following powers and duties:

1/ Assists the Commissioner in organizing, directing and coordinating the activities of the Commission;

2/ perform duties specifically assigned to him by the Commissioner;

3/ Act on behalf of the Commissioner on his absence.

**9. Establishment**

The National Sports Council (hereinafter "the Council") is hereby established.

## ፲. የምክር ቤቱ አባሎች

፩/ ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ......ሰብሳቢ፣

ለ) ሚኒስትሩ ………………ምክትል ሰብሳቢ፣

ሐ) የሚኒስቴሩ የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ……………………….…..አባል፣

መ) የሠላም ሚኒስቴር ተወካይ ……….አባል፣

ሠ) የትምህርት ሚኒስቴር ተወካይ ……አባል፣

ረ) የጤና ሚኒስቴር ተወካይ …………አባል፣

ሰ) የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ …………………አባል፣

ሸ) የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ተወካይ ………………………………………አባል፣

ቀ) የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ተወካይ………………………………አባል፣

በ) የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተወካይ……………………………..አባል፣

ተ) የገቢዎች ሚኒስቴር ተወካይ ………አባል፣

ቸ) የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ተወካይ …አባል

ኀ) የክልል ስፖርት ምክር ቤት ሰብሳቢዎች /ምክትል/ ሰብሳቢዎች …………..አባላት፣

ነ) የከተማ አስተዳደር ከንቲባዎች ተወካይ …………………………………..አባላት፣

ኘ) የክልልና ከተማ አስተዳደር የስፖርት ኮሚሽን ቢሮ ኃላፊዎች ……..…..አባላት፣

አ) የአገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ፕሬዚዳንቶች ……………………አባላት፣

ከ) የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ………..አባል፣

ኸ) ለኮሚሽኑ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ዋና ዳይሬክተሮች ……………………አባላት፣

ወ) ኮሚሽነሩ …………………………ፀሐፊ፡፡

## 10. Members of the Council

1/ The Council shall have the following members:

a) Chairperson……………...to be appointed by prime minister;

b) The Minister, -------deputy-Chairperson;

c) The State Minister of Sport sector of the Ministry --…………………..---Member;

d) The representative of the Ministry of Peace, ……………..----------Member;

e) The representative of the Ministry of Education,--………………..--- Member;

f) The representative of the Ministry of Health,-----……………….------Member;

g) The representative of the Ministry of Women, Children and Youth,--Member;

h) The representative of the Ministry of National Defense,….…………Member;

i) The representative of the Ministry of Science and Higher Education,--- ………………………………...Member;

j) The representative of the Ministry of Urban Development and Construction, -- ………………………………...Member;

k) The representative of the Ministry of Revenues, ……………………..Member;

l) The representative of the Federal Police Commission, …………………Member;

m) Chairpersons or Vice Chairpersons of Regions Sports Councils…… Members;

n) The representative of the City Administrative, Mayors …….Members;

o) Regions and City Administrative Sport Commissioners……………. Members;

p) National Sports Associations, Presidents …………………..…………...Members;

q) Ethiopian Trade Unions Confederations, President ……………………Members;

r) Executive Organs Accountable to the Commission, Director generals,…...…… … ……………………………Members;

s) The Commissioner ……………Secretary.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ እንዳስፈላጊነቱ ለስፖርቱ ዘርፍ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ታዋቂ ግለሰቦችን እና የስፖርት ባለሙያዎችን በአባልነት ወይም በተሳታፊነት ሊጋብዝ ወይም ሊያሳትፍ ይችላል፡፡

## ፲፩. <u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩/ ስፖርት ስለሚስፋፋበትና ስለሚዳብርበት ሁኔታ ይመክራል፣ ሀሳብ ያቀርባል፤

፪/ በሀገር አቀፍ የስፖርት ዘርፍ ዕቅድ ላይ ይወያያል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፤

፫/ ስፖርትን በሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ሀሳብ ያቀርባል፤

፬/ ኮሚሽኑ ሊከተላቸው በሚገቡ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ይሰጣል፤

፭/ ስፖርትን በአገር አቀፍ ደረጃ ለማስፋፋትና ሕዝባዊ ለማድረግ ስፖርቱን በበላይነት ይመራል፣ያስተባብራል፤

፮/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፪/፬/ሠ/ መሠረት ኮሚሽኑ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ያፀድቃል፡፡

## ፲፪. <u>የምክር ቤት ስብሰባ</u>

፩/ ምክር ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤

፪/ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ Without the prejudice to sub article 1 of this Article, the Council may invite known individuals and sport professionals who have a vital role as a membership or participant of the Council, as may be necessary.

## 11. <u>Powers and Duties of the Council</u>

The Council shall have the powers and duties to:

1/ Deliberate on and forward proposals for the promotion of sports;

2/ Evaluate the annual sports plan and forward proposals

3/ Deliberate on and forward recommendations on policy issues to be submitted to the government relating to sports;

4/ Give direction for Commission on strategic issues;

5/ Ensure overall organization and management of sport is community based;

6/ Approve directives to be issued by the Commission pursuant to Article 32/4/ of paragraph E of the Proclamation.

## 12. <u>Meeting of the Council</u>

1/ The Council shall hold regular meetings twice every year, provided, however, it may hold an extraordinary meeting whenever necessary up on the call of the Chairperson.

2/ There shall be quorum where more than half of members of the Council are present at any meeting;

3/ Decision of the Council shall be passed by majority votes; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without the prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own procedure.

**፲፫. በጀት**

የኮሚሽኑ በጀት ፡-

፩/ ከመንግሥት የሚመደብ በጀት፤ እና

፪/ ከሌሎች የገቢ ምንጮች፤

ይሆናል፡፡

**፲፬. የሂሳብ መዛግብት**

፩/ ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**፲፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ታህሳስ ፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

አብይ አህመድ(ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**13. Budget**

The budget of the Commission shall be:-

a/ allocated by the government and

b/ from other income sources.

**14. Books of Account**

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Commission shall be audited annually by the Federal Auditor General or by Auditors assigned by him.

**15. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on this 15th day of December, 2018, approved by the Council of Ministers.

**Done at Addis Ababa, this 21st day of January, 2019.**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**